የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፷፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፴ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 62
ADDIS ABABA 6th August 2013


## ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፪፻፺፫/፪ሺ፭ ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..................ገፅ ፮ሺ፱፻፺፭


## CONTENTS


**Regulation No. 293/2013**

Ethiopian Water Technology Institute Establishment Council of Ministers Regulation.................................. Page 6995


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፫/፪ሺ፭

## የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፭ እና አንቀፅ ፴፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፫/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

፩/ "የውሃ ቴክኖሎጂ" ማለት ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል ውሃ መገኛን ለመፈለግ፣ ለመገንባት፣ ለማምረት እና ለማሰራጨት እንዲሁም የመጠጥ ውሃና ፍሳሽ፣ የመስኖ አገልግሎትና የውሃ ኃይል ተቋማት ኦፐሬሽንና ጥገናን በሚገባ ለማስተዳደር በተግባር ላይ የሚውል ቴክኖሎጂ ነው፣

፪/ "የውሃ ልማት" ማለት የውሃ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል ውሃ የማልማት ሥራ ነው፣

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No.293/2013

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE ETHIOPIAN WATER TECHNOLOGY INSTITUTE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 35 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 (as amended).

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Water Technology Institute Establishment Council of Ministers Regulation No. 293/2013".

2. **Definitions**

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "water technology" means technology applied for water source identification, development, production and distribution of water for various uses as well as technology applied to administer properly the operation and maintenance of water supply and sewerage, irrigation and hydropower schemes;

2/ "water development" means activity executed using water technology to develop water for different uses;


ያንዱ ዋጋ
Unite Price 5:80

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፫/ "የውሃና ተዛማጅ ሥራዎች" ማለት የውሃ ልማትና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው እንደ ውሃ አቅርቦትና መስኖ ተቋማት ጥገና፣ የውሃ ጉድጓድ መቆፈሪያዎችና የኤሌክትሮ ሜካኒካል መሳሪያዎች ጥገና እና ሌሎች መሰል ተግባራት ናቸው፤

፬/ "ስልጠና" ማለት ከውሃ ልማት ጋር በተያያዘ በዘርፉ ለተሰማሩና ወደፊት ለሚሰማሩ ሰልጣኞች የሚሰጥ መደበኛና አጫጭር ተግባር ተኮር ስልጠና ነው፤

፭/ "ሚኒስቴር" ማለት የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ነው፤

፮/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) በሕግ የሰውነት መብት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

## ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

## ፭. የኢንስቲትዩቱ ዓላማ

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ በውሃ ልማት እና ተያያዥነት ባላቸው ዘርፎች ለተሰማሩ ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግርን ተደራሽ ማድረግ፤

፪/ በዘርፉ የተሰማራውንና የሚሰማራውን የሰው ሃይል ከሌሎች በዘርፉ ሙያ ከሚያሰለጥኑ የቴክኒክና ሙያ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በጋራ በመስራት በተግባር ተኮር ስልጠና ማብቃት፤ እና

፫/ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሚፈለጉ አሰልጣኞችን ማፍራትና አቅም መገንባት፡፡

## ፮. የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ከዓለም አቀፍ አሰራር አንጻር የተለዩ የክህሎት ክፍተቶችን ለመሙላት በሥራ ላይ በተለያዩ ደረጃዎች ለተሰማሩ የውሃና ተዛማጅ ስራዎች ባለሙያዎች አጫጭር ተግባር ተኮር ስልጠና በመስጠት ማብቃት፤

3/ "water and related activities" means activities of water development and those related activities such as water supply and maintenance of irrigation schemes, maintenance of drilling machineries and electro-mechanical equipment and other related activities;

4/ "training" means a regular and short-term practical training provided to the existing and potentially joining manpower of the sector in relation to water development;

5/ "Ministry" means the Ministry of Water, Irrigation and Energy;

6/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Establishment

1/ The Ethiopian Water Technology Institute (hereinafter the "Institute") is hereby established as an autonomous federal government office having its own legal personality.

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

## 4. Head Office

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

## 5. Objectives

The Institute shall have the objectives to:

1/ facilitate the transfer of technology to those engaged in water development and related activities;

2/ provide practical trainings to capacitate the existing and potentially joining manpower of the sector in cooperation with other technical and vocational education and training institutions and higher education instutuion; and

3/ produce and build capacity of instructors required by technical and vocational education and training institutions.

## 6. Powers and Duties of the Institute

The Institute shall have the powers and duties to:

1/ prepare and conduct short-term practical trainings on courses designed as per international methods to fill identified skill gaps of manpower working at different levels in water development and related activities;

፪/ በዘርፉ በአገር ውስጥ ማሟላት የማይቻለውን ክፍተት ለማሟላት የሚያስችል የቴክኖሎጂ ሽግግር ማምጣት፤

፫/ ከዘርፉ የሙያ ደረጃዎችና ከአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ጋር በተያያዘ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በሚሰጡ ተቋማት መምህራን ዘንድ ያሉ ክፍተቶችን ለመሙላት አጫጭር ተግባር ተኮር የአሰልጣኝ ስልጠናዎች መስጠት፤

፬/ በዘርፉ የትምህርትና ስልጠና ፍላጎት መሰረት በውሃና ተዛማጅ ስራዎች ላይ በሚሰሩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሚፈለጉ መምህራንን ማፍራት፤

፭/ በዘርፉ የሰው ኃይል ፍላጎት መሠረት በሀገሪቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የብቃት ማዕቀፍ ከፍተኛ ደረጃ ፕሮግራሞች ላይ የረጅም ጊዜ ስልጠና መስጠት፤

፮/ የውሃ ሀብት ልማትን ለማሳደግ የሚረዱ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ማከናወን፤

፯/ በዘርፉ ተፈላጊ ባለሙያዎችን ለሚያፈሩ የትምህርትና የስልጠና ተቋማት የስልጠና ፕሮግራሞች ማደራጀትና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ ረገድ የቴክኒክና የምክር ድጋፍ መስጠት እና የብቃት ምዘና ማዕከል አገልግሎት መስጠት፤

፰/ በሌሎች ተቋማት ያሉ ክፍተቶችን በመለየት የዘርፉን ስፔሻላይዝድ ላብራቶሪ በማደራጀት አገልግሎት መስጠት፤

፱/ በዘርፉ የሚፈለገውን የሰው ኃይል ልማት በተመለከተ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ተባብሮ መስራት፤ በጋራ ምርምሮችን በማካሄድ በዘርፉ የአገር ውስጥ የምርምር አቅም እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲጠናከር ማገዝ፤

፲/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግስት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ ማስከፈል፤

፲፩/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

፲፪/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን።

፯. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፦

፩/ አማካሪ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ አንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤ እና

፫/ አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

2/ facilitate the transfer of technology that enable to fill the local gaps in the sector's development;

3/ conduct short-term practical trainings of trainers on courses designed in line with the sector's qualification levels and new technologies to fill identified skill gaps of instructors working in technical and vocational education and training institutions;

4/ produce instructors required by the technical and vocational education and training institutions that train in water and water related professions based on the demand of the sector's education and training;

5/ conduct long-term training as per national technical and vocational education and training qualification framework on higher level programs in accordance with the manpower requirement of the sector;

6/ conduct studies and researches that facilitate the growth of water resource development;

7/ provide technical and consultation support to education and training institutions that produce graduates required by the sector in organizing training program and introduction to new technologies; and serve as center for professional competence evaluation;

8/ establish and provide specialized laboratory services by identifying the gaps of other institutions operating in the sector;

9/ cooperate with higher education institutions on human resource development in the sector; conduct joint research and assist in strengthening of local research and technology transfer capacity in the sector;

10/ charge fees for the services it renders in accordance with the rate approved by the government;

11/ own property, enter into contracts and sue and be sued in its own name;

12/ perform such other related activities as are conducive to the attainment of its objectives.

7. **<u>Organization of the Institute</u>**

The Institute shall have:

1/ an Advisory Council (hereinafter the "Council");

2/ a Director General and as may be necessary, a Deputy Director General, to be appointed by the government; and

3/ the necessary staff.

፰. **የምክር ቤቱ አባላት**

ምክር ቤቱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል። ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

፱. **የምክር ቤቱ ተግባራት**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ኢንስቲትዩቱ በሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ ያማክራል፤

፪/ የውሃ ልማትን ለማፋጠን በኢንስቲትዩቱ የተዘጋጁ ስትራቴጂዎችን፣ እቅዶችን፣ ጥናቶችን እና ምርምሮችን ገምግሞ አስተያየት ይሰጣል፤

፫/ በኢንስቲትዩቱ የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮች ላይ አስተያየት ይሰጣል፤

፬/ የኢንስቲትዩቱን የእቅድ አፈፃፀም በየሦስት ወሩ በመገምገም አስተያየት ይሰጣል።

፲. **የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**

፩/ ምክር ቤቱ በየሦስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

፪/ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

፫/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፲፩. **የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

8. **Members of the Council**

Members of the Council, including the Chairperson, shall be designated by the government; and their number shall be determined as may be necessary.

9. **Duties of the Council**

The Council shall have the duties to:

1/ advice the Institute on its activities;

2/ review and forward its recommendation on strategies, plans, studies and researches formulated by the Institute with the view to facilitate the water development;

3/ forward its opinion on capacity building programs of the Institute;

4/ evaluate the performance report of the Institute every three months and forward its opinion.

10. **Meetings of the Council**

1/ The Council shall meet every three months; provided, however, that it may hold extraordinary meetings at any time as may be necessary.

2/ There shall be quorum where more than half of the members of the Council are present at a meeting.

3/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Council may adopt its own rules of procedure.

11. **Power and Duties of the Director General**

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Institute and shall, subject to the general direction of the Ministry, direct and administer the activities of the Institute.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Institute specified under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees engaged in support services of the Institute in accordance with the federal civil service laws and, in the case of professionals engaged in the core functions of the Institute, in accordance with directive approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

ሐ) የኢንስቲትዩትን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች የኢንስቲትዩቱ የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

**፲፪. በጀት**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

**፲፫. የሂሣብ መዛግብት**

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

**፲፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፴ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

c) prepare and submit to the Ministry the strategic plan, annual plan, work program and budget of the Institute and implement same up on approval;

d) effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Institute;

e) represent the Institute in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Institute.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Institute to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Institute.

**12. Budget**

The Institute's budget shall be allocated by the government.

**13. Books of Accounts**

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or an auditor designated by him.

**14. Effective Date**

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa this 6th day of August, 2013.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**